*ለማን አቤት ይሏል*

ፈጣሪ ምህረትህ ፍቅርህ አዘንብሎ
የሲቃ ዕለቅሶችን አልሰማህ ብሎ
በዕርዛት አርጩሜ በርሃብ ቸነፈር
ነፃነት ተገፈን በባርነት ቀንበር
ከሰው ተራ ወጥተን
የአፍሪካ ማፈሪያ እስከመባል ደርሰን
ሀፍረትና ውርደት ሸንፈት ተከናንበን
ቧጭረን - አናደማ - ጥፍራችን ተነቅሏል
ጮኸን አናሰማ - ድምፃችንም ሰሏል
ፍቅርና አንድነት ጥርጣሬን ለብሰው
ላይደማመጡ እንደ ኖህ ዘመን ሰው
ቋንቋቸው ለየቅል ሆኖ ያንድ አገር ህዝብ
አልገናኝ ብሎ ሁሉም ልብ - ለልብ
ቂም በቀል አርግዞ ህይወት ለከራማ
ለየብቻ ትግል ሁሉም ላንድ አላማ
የቋጠርነው ሁሉ አጥብቀን ይላላል
ከጠላት ጋር አብሮ ጊዜውም አብሏል
ታዲያ ጌታየ ለማን አቤት ይሏል
ይህን ሁሉ መድሎ
ፍትህ ቀን ለሰጠው ሚዛኑ አዘንብሎ!!
አረ ይቅር በለን
አረ በቃ በለን
ምህረት አትንፈገን እንጀትህ ይራራ
ሰላም አውርድልን የብርሃን ጮራ!!

በሚደርስብን ግፍና በደል ተማርረን
እንደ ጨው ዘር ተበትነን
በስደት ለመኖር ተገደን
የተሳፈርንበት መርከብ
በማዕበል ሲዋከብ
ተገፍትሮ በወጀቡ
ሲገለበጥ መርከቡ
በዕሬሳ ስንሞላው ዕውቂያኖሱን
በዕግርም ስንሰደድ እያቋረጥን የብሱን
በየፈፋው ወድቀን በየጥሻው ሥራቻ
ስንሆን የዱር አውሬ መጫወቻ
አለያም ታፍነን ፣ተገርፈ ተወግረን
ወይ መዳረሻችን እንደጠፋ ቀርተን
ወይንም ተገድለን ተጥለን በጅምላ
ባንድ ስንቀበር ጉድጓድ ስንሞላ
አለያም መንገድ ላይ ዕሬሳችን ወድቆ
አክላችን ፈርሶ አጥንታችን ደቅቆ

**ጥቁር ደም አፍስሰን**
**የደም ጎርፍ አጉርፈን**
**መሬቱን አቅልተን**